**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

የፈተናው ዓይነት፦ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

የፈተናው ወቅት: የ2019 ዓ.ም. የክረምት ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 022284**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ (6)**

# ታሪክ

## ለአዲስ ገቢዎች

**ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች**

א.<u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב.<u>የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና አራት ምዕራፎችን ይዟል። ከእያንዳንዱ ምዕራፍ <u>አንድ</u> ጥያቄ መልስ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — (1x25) — | 25 ነጥብ | |
| ምዕራፍ ሁለት | — (1x25) — | 25 ነጥብ | |
| ምዕራፍ ሦስት | — (1x25) — | 25 ነጥብ | |
| ምዕራፍ አራት | — (1x25) — | 25 ነጥብ | |
| | በአጠቃላይ — | 100 ነጥብ | |

**<u>ልብ በል</u>፦ ተስማሚ ፈተና** (מבחן מותאם) **የተፈቀደላቸው** ተማሪዎች <u>ሦስት</u> ጥያቄዎችን ይመልሱ፦ ከምዕራፍ አንድ **<u>ወይም</u>** ከምዕራፍ ሁለት አንድ ጥያቄ፣ ከምዕራፍ ሦስት አንድ ጥያቄ እና ከምዕራፍ አራት አንድ ጥያቄ።

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

እንደ <u>ንድፍ</u> (<u>טיוטה</u>) መጻፍ የምትፈልገውን በሙሉ (ርዕሶችን፣ ስሌቶችንና የመሳሰሉትን) <u>በፈተና ደብተሩ ላይ ብቻ</u>፣ በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ። በእያንዳንዱ የንድፍ ገጽ ላይ "ንድፍ" ብለህ ከላይ ጻፍ።

ማንኛውንም ንድፍ በሌላ ወረቀት ላይ ስትጽፍ ከተገኘህ ፈተናህ ውድቅ ሊሆን ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢቀርቡም ቅሉ ለሴትም ለወንድም ተፈታኞች ያገለግላሉ።**

**መልካም ዕድል!**

**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: חורף תשע"ט, 2019

**מספר השאלון: 022284**

**תרגום לאמהרית (6)**

# היסטוריה

## לעולים חדשים

**הוראות לנבחן**

א. <u>משך הבחינה</u>: שעתיים וחצי.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה ארבעה פרקים. ענה על שאלה <u>אחת</u> מכל פרק.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | — | (25x1) | — 25 נקודות |
| פרק שני | — | (25x1) | — 25 נקודות |
| פרק שלישי | — | (25x1) | — 25 נקודות |
| פרק רביעי | — | (25x1) | — 25 נקודות |
| | | סה"כ | — 100 נקודות |

**<u>שים לב:</u>** תלמידים **שאושר להם מבחן מותאם** יענו על <u>שלוש</u> שאלות: שאלה אחת מפרק ראשון **<u>או</u>** מפרק שני, שאלה אחת מפרק שלישי ושאלה אחת מפרק רביעי.

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב <u>כטיוטה</u> (ראשי פרקים, חישובים וכדומה). רשוֹם "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה.

רישום טיוטות כלשהן על דפים שמחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

**בהצלחה!**

# ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ (25 ነጥብ)

### የመጀመሪያው ወቅት፦ ብሔርተኝነት በእስራኤልና በሕዝቦች ዘንድ — ከጅማሬው እስከ 1920

ከ1-3 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**1. የብሔርተኝነት እንቅስቃሴዎች (התנועות הלאומיות)**

ሀ. የአንድን ብሔር የጋራ መለያዎች አቅርብ። (10 ነጥብ)

ለ. በአውሮፓ ውስጥ በ19ነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለብሔርተኝነት እንቅስቃሴዎች መለምለም መንስዔ የሆኑትን ሦስቱን አብራራ። (15 ነጥብ)

**2. ሔርጼል (הרצל)**

ሀ. "የይሁዳዊያን አገር" በሚለው የሔርጼል መጽሐፍ መሠረት የይሁዳዊያን ችግር ምን እንደሆነ እና መፍትሔው ምን እንደሆነ አብራራ። (12 ነጥብ)

ለ. የኡጋንዳ ዕቅድ ምን ነበር፦ ዕቅዱን ያወጣው ማን ነው? ይዘቱስ ምንድን ነው? ሔርጼል ይህን ዕቅድ የደገፈው ለምን እንደሆነ አብራራ። (13 ነጥብ)

**3. ምድረ እስራኤል ከ1882–1914 ባሉት ዓመታት**

ሀ. ከ1882-1914 ባሉት ዓመታት አዲስ ገቢዎች በ**ሠፈራ** ዘርፍ የነበሩባቸውን ችግሮች አብራራ። እነዚህን ችግሮች የተቋቋሙባቸውን አንድ መንገድ አቅርብ። (13 ነጥብ)

ለ. የዕብራይስጥ ቋንቋን ለማጠናከር ኤሊዔዘር ቤንይሁዳ ያደረጋቸውን ሁለት ድርጊቶች አቅርብ እና የእነዚህን ድርጊቶች አስፈላጊነት አብራራ። (12 ነጥብ)

ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል ►

## ምዕራፍ ሁለት (25 ነጥብ)

### ሁለተኛው ወቅት፦ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል (ከ1920-1939)፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የይሁዳውያን ሠፈራ በምድረ እስራኤል

ከ4-6 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ <u>አንዱን</u> መልስ።

**4. <u>ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የቨርሳይ ውል እና ፓለቲካዊ ለውጦች</u>**

**አ.** ከ"ቨርሳይ ውል" አንቀጾች ውስጥ <u>ሁለቱን</u>፦ አንድ ከ**ጦር ኃይል** ዘርፍ እና አንድ ከ**ኢኮኖሚ** ዘርፍ አቅርብ እና የዚህን ውል <u>አንድ</u> ዓላማ አብራራ። (14 ነጥብ)

**ב.** ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓው ፖለቲካዊ ካርታ ላይ የተካሄዱትን <u>ሦስት</u> ለውጦች አቅርብ። (11 ነጥብ)

**5. <u>በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል የይሁዳዊያን ሠፈራ በምድረ እስራኤል</u>**

**አ.** በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መካከል ወደ እስራኤል አገር ለመምጣት (עלייה) ምክንያት ከሆኑት <u>ሁለቱን</u> አብራራ። (10 ነጥብ)

**ב.** በዚህ ወቅት የነበሩትን አዲስ ገቢዎች መለያዎች አቅርብ።
ከጠቀስካቸው መለያዎች ውስጥ <u>አንዱ</u> በዚህ ወቅት በእስራኤል አገር በነበረው <u>አንድ</u> የአሠፋፈር ቅርጽ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ አብራራ። (15 ነጥብ)

**6. <u>በአሥራ ዘጠኝ ሠላሳዎቹ ዓመታት ይሁዳዊያን፣ ዓረቦች እና ብሪታንያዊያን በእስራኤል ሀገር</u>**

**አ.** ለ"מרד הערבי" (1936) መንስዔ ከሆኑት <u>ሁለቱን</u> አብራራ እና ለዚህ "מרד הערבי" ምላሽ ደህንነትን ለማጠናከር የይሁዳዊያን ሠፈራዎች ያደረጓቸውን <u>ሁለት</u> ድርጊቶች አቅርብ። (15 ነጥብ)

**ב.** የ"ፒል ኮሚሽን"ን (1937) ምክሮች (המלצות) አቅርብ። (10 ነጥብ)

ገጽ 4 ላይ ይቀጥላል ▶

## ምዕራፍ ሦስት (25 ነጥብ)

**ሦስተኛው ወቅት፦ አምባገነኑ መንግሥት (המשטר הטוטליטרי)፣ ናዚነት፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነትና የይሁዳውያን መጨፍጨፍ (השואה)**

ከ7-10 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ <u>አንዱን</u> መልስ።

**7. <u>የናዚዎች ርዕዮተ-ዓለም ከ1933-1938 ባሉት ዓመታት (המשטר הנאצי בגרמניה בשנים 1938-1933)</u>**

**ሀ.** የናዚ ርዕዮተ-ዓለምን (אידאולוגיה) መሪ ሕግ አብራራ እና ሂትለር ይህንን ሕግ በጀርመን ውስጥ ለማስካሄድ ያደረጋቸውን <u>ሁለት</u> ድርጊቶች አቅርብ። (12 ነጥብ)

**ለ.** ከ1933-1938 ባሉት ዓመታት ውስጥ በጀርመን በነበሩ ይሁዳዊያን ላይ የናዚ ርዕዮተ-ዓለምን <u>ሁለት</u> ዓላማዎች አብራራ እና ካብራራሃቸው ዓላማዎች <u>አንዱን</u> ለማሳካት ጀርመኖች ያደረጉትን <u>አንድ</u> እርምጃ አቅርብ። (13 ነጥብ)

**8. <u>ማጎሪያዎቹ (הגטאות)</u>**

**ሀ.** ናዚዎቹ ማጎሪያዎቹን ለምንድን ነው ያቋቋሟቸው? <u>ሁለት</u> ምክንያቶችን አቅርብ። (12 ነጥብ)

**ለ.** ይሁዳዊያን "የመጨረሻው መፍትሔ" እስኪፈጸም <u>ድረስ</u> የማጎሪያዎቹን የሕይወት ሁኔታዎች ለመቋቋም የሞከሩባቸውን <u>ሦስት</u> መንገዶች አቅርብ። (13 ነጥብ)

**9. <u>በናዚዎች ከተወረሩ አገራት በይሁዳዊያን ላይ ያላቸው አመለካከት (היחס אל היהודים בארצות הכיבוש הנאצי)</u>**

**ሀ.** የአካባቢው ማኅበረሰብ በናዚዎች በተወረሩ አገራት ባሉ ይሁዳዊያን ላይ ላላቸው አመለካከት ምክንያቱን አብራራ፦
<u>ሁለት</u> ምክንያቶች ከናዚዎች ጋር ለተባበሩት እና <u>ሁለት</u> ምክንያቶች ዝም ብለው ለሚመለከቱት (העומדים מן הצד) አቅርብ። (13 ነጥብ)

**ለ.** "חסיד אומות העולם" የተባለውን መረጃ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች አቅርብ።
ከተማርከው "חסיד אומות העולם" <u>አንድ</u> ምረጥ እና ድርጊቶቹን አሳይ።
(12 ነጥብ)

**10. <u>የማጎሪያዎቹ አመጻ (המרד בגטאות)</u>**

**ሀ.** የማጎሪያው አመጸኞች ዓላማዎች ምን ምን ነበሩ?
ለአማጺያኑ ከነበሯቸው ማመንታቶች (דילמות) መካከል <u>ሁለቱን</u> አብራራ።
(15 ነጥብ)

**ለ.** የቫርሻ ማጎሪያ አመጻን አስፈላጊነት አብራራ። በመልስህ ላይ ለዚህ አመጻ አስፈላጊነት <u>ሁለት</u> ምክንያቶችን አቅርብ። (10 ነጥብ)

ገጽ 5 ላይ ይቀጥላል ►

## ምዕራፍ አራት (25 ነጥብ)

### አራተኛው ወቅት፦ እስራኤል ሀገርን በመካከለኛው ምስራቅ መገንባት

ከ11-14 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ አንዱን መልስ።

**11. የሀገረ-እስራኤል ጥያቄ - በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት**

 አ. ብሪታንያ ሀገረ-እስራኤል የሚለውን ጥያቄ ወደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንድታስተላለፍ ተጽዕኖ ያደረገባትን አንድ ምክንያት አብራራ እና ኅዳር/ኖቬምበር 29 ቀን 1947 (כ"ט בנובמבר) የተወሰነውን የተባበሩት መንግሥታትን ዋና ውሳኔ አቅርብ። (15 ነጥብ)

ለ. በኅዳር/ኖቬምበር 29 ቀን 1947 (כ"ט בנובמבר) ምርጫ ላይ የሶቪየት ኅብረት አቋም ምን ነበር? "ቀዝቃዛው ጦርነት" በዚህ አቋም ላይ ያደረገውን ተጽዕኖ አብራራ። (10 ነጥብ)

**12. በአሥራዘጠኝ ሃምሳዎቹ እና በአሥራዘጠኝ ስልሳዎቹ ወደ እስራኤል ሀገር መግባት (עלייה) እና መስተንግዶ**

አ. በአሥራዘጠኝ ሃምሳዎቹ እና በአሥራዘጠኝ ስልሳዎቹ ዓመታት የእስራኤል አገር የኢኮኖሚ ጉዳይ በአዲስ ገቢዎች መስተንግዶ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳደረገ አብራራ።
በዚህ ወቅት በአዲስ ገቢዎች መስተንግዶ ላይ ተጽዕኖ ያደረገውን ተጨማሪ ምክንያት አቅርብ።
(13 ነጥብ)

ለ. በአሥራዘጠኝ ሃምሳዎቹ እና በአሥራዘጠኝ ስልሳዎቹ ዓመታት በአዲስ ገቢዎች ላይ የነበሩባቸውን ሁለት ችግሮች አቅርብ።
ይህ ወደ እስራኤል አገር መግባት እስራኤል አገርን እንዴት እንዳጠናከራት አብራራ። (12 ነጥብ)

**13. የእስራኤል ማኅበረሰብ ለ"ሾአ"ያለው አመለካከት (יחס החברה הישראלית לשואה)**

አ. የ"አይክማን" ፍርድ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የእስራኤል ማኅበረሰብ ከ"ሾአ" በተረፉት ላይ የነበራቸውን አመለካከት አሳይ እና ለዚህ አመለካከት ምክንያት ከሆኑት አንዱን ጥቀስ።
(15 ነጥብ)

ለ. የእስራኤል ማኅበረሰብ ለ"ሾአ" ባለው አመለካከት ላይ የ"አይክማን" ፍርድ ያመጣቸውን ሁለት ተፅዕኖዎች አብራራ። (10 ነጥብ)

**14. የስድስቱ ቀን ጦርነት/ የአስተሰርዮ ጦርነት (מלחמת ששת הימים / מלחמת יום הכיפורים)**

ከሁለቱ ጦርነቶች አንዱን ምረጥ፦ የስድስቱ ቀን ጦርነት (1967) ወይም የአስተሰርዮ ጦርነት (1973)።

አ. ለመረጥከው ጦርነት መንስኤ ከሆኑት ውስጥ ሁለቱን አብራራ። (12 ነጥብ)

ለ. የመረጥከው ጦርነቱ **በእስራኤል ሃገር** በማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዘርፍ ያደረገውን ተጽዕኖ እና ጦርነቱ **በዓረብ አገራት** ላይ ያደረገውን ተጽዕኖ አብራራ። (13 ነጥብ)

**መልካም ዕድል!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።

**בהצלחה!**

זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך